# የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

# ፋይናንሽያል ሪፖርት አቅራቢ አካላት ምዝገባ መረጃ

ሰኔ 2009 ዓ.ም

1. **መግቢያ**

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብን ለመቆጣጠር በደንብ ቁጥር 332/2007 የተቋቋመ የመንግስት መስሪያ ቤት ሲሆን፣ በአዋጁ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (2)(መ) ከተሰጡት ተግባርና ሀላፊነቶች መካከል የሪፖርት አቅራቢ አካላትን የህዝብ ጥቅም ያለባቸው እንዲሁም አነስተኛና መካከለኛ በሚል መለየት የሚያስችል መስፈርቶችን በማውጣት የሚመዘግብ መሆኑን ያስቀምጣል፡፡

በተጨማሪም በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ (1) ሪፖርት አቅራቢዎች የሂሳብ መግለጫዎቻቸውን ኦዲት በማስደረግ ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለባቸው፣ እንዲሁም ቦርዱ እነዚህን ሪፖርቶች በአንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (2)(ሸ) የመገምገምና ፍላጎት ላላቸው ባለድረሻ አካላት ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ በአንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ (4) እንደሚያመቻች ይደነግጋል፡፡ የሪፖርት አቅራቢ አካላትን መመዝገብ እና ሪፖርቶቻቸውን ለቦርዱ እንዲያስገቡ ማድረግ ያስፈለገበት ፋይናንስ ሪፖርት የተሟላ ፣ግልጽና በቀላሉ ሊረዱት የሚያስችል ፣ ተጠያቂነት በማጎልበት የሕዝብን ጥቅም የሚያስጠብቅ እንዲሆን ታስቦ አገራችን የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎችን ተከትሎ የተዘጋጁ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡

2. **ዓላማ**

ሪፖርት አቅራቢ አካላት እንዲመዘገቡ በማድረግ በአዋጁ አንቀፅ 847/2006 አንቀጽ 8 መሠረት ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሂሳብ መግለጫዎችን ለቦርዱ ማቅረብ እንዲችሉ ለማመቻቸትና ለቦርዱ የሚቀርበውን የሂሳብ ሪፖርት ኦርጂናል ቅጂ በሌላ ሕግ ሥልጣን ለተሰጣቸው የመንግስት አካላት ከሚያቀርቡት ጋር ወጥነት ያለው እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

3. **ምዝገባው ማንን ይመለከታል?**

ምዝገባው በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 18 መሰረት ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሆኑትን በሙሉ የሚያካትት ሲሆን፣ ይኸም የመንግስት መስሪያ ቤቶችንና ቦርዱ ባወጣው የመጠን መስፈርት መሰረት እንደ ጥቃቅን ድርጅት የሚቆጠሩትን

ሳይጨምር ማንኛውም በሕግ የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ያለባቸውን አካላት የሚያካትት ነው።

በአጠቃላይ የሪፖርት አቅራቢ አካላት የህዝብ ጥቅም ያለባቸው ድርጅቶች (Public Interest Enities) እና አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች በሚባሉ ሁለት ዋና ምድቦች የሚመደቡ ሲሆን፣ በሁለቱም ምድብ ስር የሚወድቁ ሪፖርት አቅራቢ አካላት ለየምድቡ የተዘጋጁትን ተገቢ ቅጾች በመጠቀም የምዝገባ ማመልከቻዎችን በመሙላት የሚመዘገቡ ይሆናል ።

## 3.1.<u>**የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው**</u> (Public Interest Entities) **አካላት**

በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 17 መሰረት "**የሕዝብ ጥቅም ያለበት አካል**" ማለት የስራውን ዓይነት ወይም ባህሪ፣ የሀብቱን መጠን ወይም የሰራተኛውን ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት ቦርዱ ከህዝብ ጥቅም ጋር ከፍተኛ ትስስር አለው ብሎ የሚወስነው ሪፖርት አቅራቢ አካል ሲሆን፣ በተለይም የሚያወጣውን የግዴታ ምስክር ወረቀት ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለግብይት ማዋል የሚችል ማንኛውንም ኩባንያን፣ ባንኮችን፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን እና ማንኛውንም ሌሎች የፋይናንስ ተቋማትን እና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን እንደሚጨምር ይገልጻል። በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሪፖርት አቅራቢ አካላት የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት (Public Interest Enities) ናቸው፦

- 3.1.1. ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋሞች፣ የቁጠባ ሂሳብ የሚያንቀሳቅስ ማንኛውም ተቋም፣ የካፒታል ቁሳቁሶችን ፋይናንስ የሚያደርግ ማንኛውም ድርጅት እንዲሁም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር የሚደረግበት ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም፤
- 3.1.2. የሚያወጣው የግዴታ ወይም የአክሲዮን የምስክር ወረቀት ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ለግብይት መዋል የሚችል ማንኛውም ድርጅት፤
- 3.1.3. አግባብ ባለው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካል ቁጥጥር የሚደረግበት ማንኛውም የጡረታ ወይም ፕሮቪደንት ፈንድ የጋራ የኢንቨስትመንት ሥራና ሌላ መሰል ተቋም፤
- 3.1.4. በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት፣

3.1.5. በኢትዮጵያ የምርት ገበያ የተመዘገበ ማንኛውም የግብይት ተዋናይ አባል ወይም አገናኝ አባል፣

3.1.6. ለፐብሊክ በግዢ የሚሰራጩ አስፈላጊ አገልግሎቶችን አቅራቢ ማንኛውም አካል፣

3.1.7. በበጎ አድራጎት እና ማህበራት ኤጀንሲ ቁጥጥር የሚደረግበትና በሕግ የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ያለበት የማንኛውም ለትርፍ ያልተቋቋመ አካል (የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት)፣

3.1.8. እንዲሁም ባለፈው የሂሳብ ዓመት (በ2008 የሂሳብ ዓመት) በተዘጋጀና ኦዲት በተደረገው የድርጅቱ የሂሰብ መግለጫ ላይ ተመስርቶ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የመጠን መስፈርቶች መካከል ቢያንስ ሁለቱን የሚያሟላ በማንኛውም ዓይነት የንግድ ሥራ የተሰማራ የግል ድርጅት፡-

   3.1.8.1. የድርጅቱ አመታዊ ገቢ ብር 50,000,000.00 (ሃምሳ ሚሊዮን) እና ከዚያ በላይ ከሆነ፣

   3.1.8.2. የድርጅቱ ተቀጣሪ ሠራተኞች ብዛት 100 እና ከዚያ በላይ ከሆነ፣

   3.1.8.3. የድርጅቱ ጠቅላላ ሀብት 100,000,000.00 (መቶ ሚሊዮን) እና ከዚያ በላይ ከሆነ፣

   3.1.8.4. የድርጅቱ ጠቅላላ ተከፋይ ሂሳብ (የባለአክስዮኖቹን ሀብት ሳይጨምር) 100,000,000.00 (መቶ ሚሊዮን) ብር እና ከዚያ በላይ ከሆነ፣

## 3.2. አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች የትኞቹ ናቸው?

በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 20 መሰረት **"አነስተኛና መካከለኛ ድርጅት"** ማለት የሕዝብ ጥቅም ላለበት አካል በተሰጠው ትርጓሜ የማይሸፈን ሪፖርት አቅራቢ አካል የሆነ እና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ውጪ ያለ ድርጅት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሪፖርት አቅራቢ አካላት አነስተኛና መካከለኛ ድርጅት ናቸው፦

3.2.1. ከላይ በአንቀጽ 3.1.8. ስር የተመለከተውን የህዝብ ጥቅም ያለበት የሪፖርት አቅራቢ አካል መስፈርት የማያሟላ ማንኛውም በኩባንያ መልክ የተመሰረተ የግል ንግድ ድርጅት

3.2.2. ለፐብሊክ ግብይት ማዋል የሚችል የግዴታ ወይም የአክሲዮን የምስክር ወረቀት ለማውጣት በዝግጅት/በሂደት ላይ ያልሆነ ማንኛውም የግል ንግድ ድርጅት፣

3.2.3. ከላይ በአንቀጽ 3.1.8. ስር የተመለከተውን የህዝብ ጥቅም ያለበት የሪፖርት አቅራቢ አካል መስፈርት የማያሟላ በርከት ላሉ ከድርጅቱ ውጪ ያሉ አካላትን ሀብት በአደራ ማስተዳደርን/መያዝን እንደ ዋነኛ/ተቀዳሚ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴው አድርጎ የማያካሂድ ማንኛውም የንግድ ድርጅት፣

3.2.4. ከላይ በአንቀጽ 3.1.8. ስር የተመለከተውን የህዝብ ጥቅም ያለበት የሪፖርት አቅራቢ አካል መስፈርት የማያሟላ አመታዊ ገቢው ብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን) እና ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም የግል ንግድ ድርጅት፣

## 4. ለምዝገባ ምን ያስፈልጋል?

- ሙሉ በሙሉ የተሞላ የተፈረመበትና ማህተም ተደርጎበት የመመዝገቢያ ቅጽ
- ለመጨረሻ ጊዜ ኦዲት የሆነው የሂሳብ መግለጫ ቅጽ
- ለመጨረሻ ጊዜ በተደረገው ኦዲት በኦዲተሩ ለማኔጅመንት የቀረበ የቁጥጥር ሪፖርት ቅጽ
- ለመጨረሻ ጊዜ አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ አካል በተደረገ የቁጥጥር ግምገማ የቀረበ የግምገማ ውጤት (የሚመለከተው ከሆነ)
- የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጽ
- የንግድ ስራ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጽ
- የግብር ከፋይ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጽ
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጽ
- የድርጅቱ መመስረቻ ጽሁፍ ቅጽ
- የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ቅጽ
- የውል ግዴታ/pledge-form ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል

5. **የምዝገባው ጊዜ**

- ከ ሰኔ 15/ 2009 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30 ይሆናል፡፡

6. **የምዝገባው ቦታ**

- በኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ዋና መስሪያ ቤት
  ጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 02፣ 6 ኪሎ አካባቢ ማዳጋስካር መንገድ፣ ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ኢንስቲትዩት ህንፃ 4ኛ ፎቅ

7. **ባለመመዝገብ የሚመጣ ኃላፊነት**

በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀፅ 4(2)(መ፤ሰ፤ሸ)እና በአንቀፅ 36(1)(ረ) መሠረት ቦርዱ የሪፖርት አቅራቢ አካላትን የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ መለየት የሚያስችል መስፈርት ማውጣት፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ተቀብሎ መመዝገብ፣ የሂሳብ መግለጫዎችን አጥጋቢነትና ትክክለኛነት የመመርመር እና መቆጣጠር እንዲሁም ደግሞ አዋጅ ቁጥር 847/2006 በዚህ አዋጅ መሠረት የወጣን ደንብ ወይም መመሪያ የሚጥስ ተግባር ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ጥሰቱን በፈጸመው ማንኛውም አካል ላይ የዲስፕሊን ክስ በመመስረት እርምጃ እንደወሰድ ሙሉ ስልጣንና ኃላፊነት ተሰቶታል፡፡

ስለሆነም ማንኛውም የሚመለከተው ሪፖርት አቅራቢ አካል ያለበትን ይህንን የህግ ግዴታ በመረዳት ወደ ቦርዱ ቀርቦ መመዝገብ ያለበት መሆኑን አበክረን እናሣስባለን፡፡

እንደ መንግስት ተቆጣጣሪ አካል የመጨረሻ ግባችን የሆነውን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ተዓማኒነት ለማረጋገጥ የሂሳብ ስራና የኦዲት አገልግሎት የጥራት ደረጃ እንዲሻሻል ለማስቻል ፣ ያንንም ለማሳካት በሕግ የተሰጠንን ስልጣን በሙሉ እንጠቀማለን፡፡

*ለበለጠ መረጃ: የቦርዱን ድረገጽ: www.aabe.gov.et*
*በስልክ ቁጥር +251-111540910 ፣+251-111540900 ፣+251-111540913 በመደወል ወይም ስድስት ኪሎ ማዳጋስካር መንገድ ሊደርሺፕ ህንጻ 4ኛ ፎቅ የሚገኘውን የቦርዱን ቢሮ በአካል በመገኘት ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡*